**NEWS LETTER**

**Published by public & International Relations Directorate of NALA**

ቅጽ 1 ቁጥር 25 ነሀሴ 2002

# በዓለም አቀፍ የቤተመጻሕፍት ፌዴሬሽን ማህበር(IFLA) ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ

# ኤጀንሲው ተሳተፈ

76ኛው የዓለም-አቀፍ የቤተመጻሕፍት ፌደሬሽን ማህበር (IFLA) ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ እ.ኤ.አ ከኦገስት 10-15/2010 በስዊድን ጉተንበርግ ከተማ ሲካሄድ በምክትል ኮሚሽነር ማዕረግ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር አቶ አትክልት አሰፋ በጉባዔው ላይ ተሳትፈዋል፡፡

የጉባዔው የመወያያ ዋና አጀንዳ “Open access to knowledge-- promoting sustainable progress” በሚል ጭብጥ ላይ ያተኮረ ሲሆን **ብሔራዊ ዓብያተ መጻሕፍት በሀገር፣ አህጉርና ዓለም-አቀፍ ደረጃ የንባብና የጽሁፍ ባህልን በማሳደግ በኩል ስለሚጫወቱት የላቀ ሚና፣ ስለዲጂታል ቤተመጻሕፍት፣ስለ ህግ ክምችት፣ ስለ ቅጅ መብትና ቤተ መጻህፍት፣ በአህጉራዊና ዓለም-አቀፋዊ ተቋማትና ድርጅቶች ስለሚገኙ የዶክመንት ቅርሶች መኖር ስለሚገባው የመረጃ ልውውጥ**

**ከቤተመጻሕፍት ተጠቃሚዎች ጋር በቅርበት የመስራት አስፈላጊነት፣የንባብ ባህሉ የዳበረ ህብረተሰብ ከመፍጠር፣ በትምህርት ቤቶች አካባቢ ዓብያተ መጻሕፍትን በመደገፍ የማስፋፋትና** በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ በቡድንና በጋራ ሰፊ ውይይት ተደርጐ ለዘመናዊ ቤተመጻሕፍት አገልግሎት አሰጣጥና ዕድገት ሊያግዙ የሚችሉ ጠቃሚ ዕውቀቶችና ልምዶች እንደተገኙ ለማወቅ ተችሏል፡፡

የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር አቶ አትክልት አሰፋ በዓለም-አቀፍ የቤተመጻሕፍት ፌዴሬሽን ማህበር በብሔራዊ ቤተመጻሕፍት ቋሚ ኮሚቴ በአባልነት ተመርጠው የሚያገለግሉ ሲሆን በዚሁ ጉባዔ ላይ በስዊድን ጉተንበርግ ዩኒቨርሲቲ አስተናጋጅነት በተዘጋጀውና የብሔራዊ ቤተመጻሕፍት ዋና ዳይሬክተሮች ብቻ በሚሰበሰቡበት ስብሰባ ላይ ተካፋይ በመሆን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ የመሠረታዊ የአሠራር ሂደት ለውጥ(BPR)ጥናት አካሂዶ በኤጀንሲው እየተገበረ ስላለው የBPR የሙከራ ትግበራ፣ ኤጀንሲው ስለሚሰጣቸው አገልግሎቶች፣ የህፃናት ቤተመጻሕፍት ለማቋቋም እየተደረገ ስላለው ጥረት፣ የአገልግሎት አሰጣጡን ዘመናዊና ቀልጣፋ ለማድረግ እየተሰራ ስላለው የአቅም ግንባታ ስራ፣ ስለተቋሙ የኔትወርክ ዝርጋታ፣ የሳውንድ አርካይቭስ ለማቋቋም ከዩኔስኮ ጋር በተደረገው ስምምነት መሠረት አስፈላጊ ዕቃዎችን ከውጭ ሀገር ለማስገባት ሥራው ስለ መጀመሩና ሌሎችንም የተቋሙን ዓበይት ተግባራት በመዘርዘር በጉተንበርግ ዩኒቨርስቲ ለተሰበሰበው የብሔራዊ ቤተመጻሕፍት ዳይሬክተሮች ገለፃ አድርገዋል፡፡

በብሔራዊ ቤተመጻሕፍት ዳይሬክተሮች ስብሰባ ላይ ከሰባ በላይ ከሚሆኑ ሀገሮች የመጡ የብሄራዊ ቤተ መጻሕፍት ዳይሬክተሮች የኢትዮጵያን ሠንደቅ ዓላማ ጨምሮ የየሀገሮቻቸውን ሠንደቅ ዓላማ ከፊት ለፊታቸው በማድረግ ውይይቱን እንደተሳተፉ ለማወቅ ተችሏል ፡፡

በጉባዔው ማጠቃለያ ላይ የጥናት ጽሑፍ በማቅረብ፣ በቡድን ውይይት ወቅት የላቀ ተሣትፎ በማድረግ ለጉባኤው መሳካት ጠቃሚ ግብአቶችን ላስገኙና በጠቅላላው በጉባኤው ላይ ተገኝተው ጉባዔውን ለተሳተፉ ተሣታፊዎች በሙሉ በጉባዔው አስተናጋጅ በኩል ከፍተኛ ምስጋና ቀርቧል፡፡

በማጠቃለል የ76ኛው የIFLA ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ጠቃሚና ፍሬያማ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ከተወያየና አንዳንድ ውሳኔዎችን ካስተላለፈ በኂላ ቀጣዩ የIFLA ዓመታዊ ስብሰባ በፖርቶሪኮ (ካሪቢአን) እንደሚካሄድ ተገልጾ የ2010 (እ.ኤ.አ) የIFLA ዓመታዊ ኮንፈረንስ ኦገስት 15 ቀን 2010 ከሰአት በኃላ ተጠናቋል፡፡

## የ2002 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ

ሐምሌ 6 ቀን 2002 ዓ.ም ለግማሽ ቀን በኤጀንሲው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ጠቅላላ የተቋሙ ሠራተኞች በተገኙበት የበጀት ዓመቱ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ቀርቦ ተገመገመ።

ሪፖርቱን ያቀረቡት የኤጀንሲው ዕቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት ጊዜያዊ ዳይሬክተር አቶ ሙስጠፋ ዑስማን ሲሆኑ ስብሰባውን የመሩት ደግሞ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር አቶ አትክልት አሰፋ ናቸው።

በበጀት ዓመቱ አምስቱን የሲቪል ሰርቪስ ንዑሳን ፕሮግራሞችን በመተግበር አሠራርን ማሻሻልና መልካም የሥራ አካባቢ ሥነ ምግባርን ከማስፈን፣ የሰው ኃብት ልማት ውጤታማ እንዲሆን ከማድረግ፣ የግዥ ፋይናንስ ንብረት አስተዳደር ሥራዎችን በማከናወን በጀትን በወቅቱ ከመጠቀም፣ የዕቅድ አፈጻጸም ኘሮግራሞችን ኦዲት በማድረግ የማረጋገጥ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የማስፋፋትና የመረጃ ሥርዓት ዝርጋታ ፕሮግራሞችን በማከናወን የተቋሙን አሠራር ዘመናዊ ከማድረግ፣ የዕቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ ከማካሄድ፣ ህግነክ ጉዳዮችን ከመከታተልና ከማስፈፀም፣ የደንበኞችን ፍላጐት በጥናት በመለየት የአገልግሎት አሰጣጥ እንዲሻሻል ከማድረግ፣ የመረጃ ሀብቶችን በማሰባሰብና በማደራጀት ለአገልግሎት ከማብቃት፣ ውጤታማ የሰው ኃይል ከመስጠት፣ በመረጃ ሀብቶች በመጠቀም በጥናትና ምርምር የዳበረ ህብረተሰብ ለመፍጠር ዓላማ-ተኮር የማስተዋወቅ ፕሮግራም ከማካሄድ፣ በሥርዓተ-ጾታና ኤች አይ ቪ/ኤድስ ላይ የመረጃ ሀብቶችን በማሰባሰብ አገልግሎት ከመስጠት ፣ከሰው ኃይል እና ፋይናንስ ዕቅድ አፈፃፀም አኳያ የተከናወኑ ተግባራት በሪፖርቱ በዝርዝር ቀርበው ውይይት ተካሂዶባቸዋል።

በበጀት ዓመቱ ሊተገበሩ ከተያዙ 251 ተግባራት ውስጥ 185 ተግባራት ከ80% በላይ የአፈፃፀም ደረጃ ያላቸው በመሆኑ በጠንካራ ጐን የታዩ ሲሆን 31 ተግባራት ከ50% በታች የአፈፃፀም ደረጃ የተመዘገበባቸው ተግባራት ችግሮቻቸው በደንብ ተለይተው በቀጣይ በጀት ዓመት በተሻለ የአፈፃፀም ደረጃ እንዲተገበሩ መጣር እንደሚያስፈልግ በሪፖርቱ እንደመፍትሔ ሃሣብ ቀርቧል። በቀረበው ሪፖርት ላይ የተለያዩ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ከሠራተኞች ቀርበው በሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎችና በውይይቱ ሰብሳቢ መልስ ተሰጥቶባቸዋል።

በበጀት ዓመቱ የተከናኑ ተግባራትን መነሻ በማድረግ የኤጀንሲው ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀም በተሻለ ደረጃ ላይ የሚገኝ ቢሆንም በሥራ አፈፃፀም የታዩ ጠንካራ ጐኖችን የበለጠ አጠናክሮ ድክመቶችን በማስወገድ ጠንክሮ መስራት እንደሚገባ አስረድተው የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት /BPR/ የሙከራ ትግበራ ተጠናቆ ወደሙሉ ትግበራ ለመግባት ኤጀንሲው በዝግጅት ላይ በመሆኑ ሠራተኛው ከአሮጌ አስተሳሰብ በመላቀቅ አዲስ የአስተሳሰብና የአመለካከት ለውጥ ማምጠት ከቻለ በቀጣይ በጀት ዓመት የተሻለና የላቀ የአፈፃፀም ደረጃ ማስመዝገብ እንደሚቻል በውይይቱ ማጠቃለያ ላይ የውይይቱ ሰብሳቢ ገልፀዋል፡፡

## የ2003 በጀት ዓመት ዕቅድ ተገመገመ

የኤጀንሲውን ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማ፣ የጋራ ዕሴቶች፣ የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት፣ የአምስት ዓመቱን ስትራቴጂክ ዕቅድና የ2002 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀምንና ከየሥራ ሂደቶች የቀረቡትን ዝርዝር ተግባራት መሠረት በማድረግ የተዘጋጀው የ2003 በጀት ዓመት ዕቅድ ነሐሴ 3 ቀን 2002 ዓ.ም ለግማሽ ቀን በኤጀንሲው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ጠቅላላ የኤጀንሲው ሠራተኞች በተገኙበት ተገመገመ፡፡

የበጀት ዓመቱን የድርጊት መርሐ-ግብር ያቀረቡት የዕቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት ጊዜያዊ ዳይሬክተር አቶ ሙስጠፋ ዑስማን ሲሆኑ ስብሰባውን የመሩት ደግሞ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ተወካይ  አቶ አህመድ አደም ናቸው፡፡

የበጀት ዓመቱ ዕቅድ በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሠረት የታቀዱ 12 ዓበይት ተግባራትን የያዘ እና ከ12ቱ ዓበይት ተግባራት የመነጨ 216 ንዑሳን ተግባራትን አካቶ የተዘጋጀ መሆኑን የበጀት ሪፖርቱ አቅራቢ ገልፀዋል፡፡ በመቀጠልም የሥራ ሂደት ቅንጅትና የቡድን ስሜት (Team Sprit) በመፍጠር ለበጀት ዓመቱ የተመደበውን ውሱን ሀብትና ጊዜ ውጤታማ በሆነ መንገድ በመጠቀም በበጀት ዓመቱ የተያዙትን የእቅድ ተግባራት በማከናወን ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚገባ ከወዲሁ አስገንዝበዋል፡፡

የ2003 በጀት ዕቅድ ዝርዝር ተግባራትን በተያዘላቸው የድርጊት መርሐ-ግብር ማከናወን ከተቻለ አሁን ያለውን የተገልጋይ ፍላጐት 48 በመቶ በማሳደግ የተገልጋይን ቁጥር በመቶ አስር

ፐርሰንት ማሳደግ እንደሚቻል የሪፖርቱ አቅራቢ አክለው ገልፀዋል፡፡ ለበጀት ዓመቱ ለታቀዱ ዝርዝር ተግባራት በቂ በጀት የማይመደብ ከሆነ ዕቅዱን ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ አንዳንድ ሥጋቶች ሊኖሩ እንደሚችሉም በገለፃው ወቅት ተጠቁሟል፡፡

በውይይቱ ወቅት የተለያዩ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ከውይይቱ ተሣታፊዎች ቀርበው ከመድረክና ከሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ማብራሪያና መልስ ተሰጥቷል፡፡

የውይይቱ ሰብሳቢ የ2003 በጀት ዓመት ዕቅድ ብዙ ያልተሟሉ ነገሮች ባሉበት ሁኔታ የተዘጋጀ ቢሆንም የሀገሪቱን ውሱን ሀብቶች በአግባቡ በመጠቀም ውጤታማ ሥራ መሥራት እንደሚቻል አስረድተው ከውይይቱም የበጀት ዓመቱን ዕቅድ ተግባራት ለማዳበር የሚያግዙ ብዙ ጠቃሚ ግብዓቶች የተገኙ መሆኑን በማስታወስ የበጀት ዓመቱን ዕቅድ ተግባራት ከBPR ጥናት የሙከራ ትግበራና ከBSC ሥልጠና ጋር አጣጥሞ መሥራት እንሚገባ በውይይቱ ማጠቃለያ ላይ አስገንዝበዋል፡፡

## የግንዛቤ ማስጨበጫ ገለፃ ተደረገ

በኤጀንሲው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ሰኔ 12 ቀን 2002 ዓ.ም ለግማሽ ቀን ለኤጀንሲው ሠራተኞች በኤጀንሲው የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂና የመረጃ ሥርዓት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት እየተሠራ ስላለው ሥራና የኔትወርክ መሠረተ-ልማት ፕሮጀክት በሥራ ሂደቱ ባለሙያዎች ገለፃ ተደረገ፡፡

ኤጀንሲው ከኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማት ኤጀንሲ ጋር በመተባበር አገር በቀል በሆነው “ሳይበር ሶፍትዌር” በተባለ ድርጅት አማካኝነት የለማው የተቀናጀ የቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት የመረጃ ሥርዓት (National Integrated Records and Library Information System) ዝግጅት ባላቸውና በፕሮጀክቱ ከተካተቱ ሃያ የፌዴራል መ/ቤቶች በአሥራ ስድስቱ መ/ቤቶች የሰው ኃይል የማሠልጠንና ሶፍትዌሩን የመጫን ተግባራት እየተከናወነ መሆኑ ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም የኤጀንሲውን አገልግሎት አሰጣጥ ሙሉ በሙሉ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን ለማድረግ ከአቅም ግንባታ ሚ/ር እና ከኢትዮጵያ ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማት ኤጀንሲ (EICTDA) ጋር በመተባበር የአቅም

ግንባታ ሥራዎች እየተሰሩ_እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ሁዋዌይ ከተባለ ትልቅና ግዙፍ የቻይና ኩባንያ ጋር በመንግሥት ደረጃ የኔትወርክ ዝርጋታ ውል ተፈጽሞ በ13 የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና በ34 ሳይቶች የኔትወርክ ዝርጋታ ጥናት 98% ተጠናቆ ለትገበራ በዝግጅት ለይ እንደ ሆነ ከገለጻው ለመረዳት ተችሏል፡፡

የኔትወርክ መሠረተ-ልማት ዝርጋታ ኘሮጀክቱ ሲጠናቀቅ በአካባቢያዊ የመረጃ መረብ መ/ቤቶችና የሥራ ክፍሎች የድምጽ፣ የምስል፣ የኢንተርኔትና የጽሑፍ መልዕክቶችንና ልዩ ልዩ የመረጃ መሣሪያዎችን በጋራ ለመጠቀም እንደሚያስችል በውይይቱ ወቅት ተብራርቷል፡፡

በተዘጋጀው የግንዛቤ ማስጨበጫ ገለፃ ላይ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችና ከመንግሥት ተቋማት የሚመጡ ተገልጋዮች የሚፈልጉትን መረጃና አገልግሎቶች በአንድ መስኮት ካሉበት ቦታ ሆነው እንዲያገኙ ለማድረግ ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል የኤጀንሲው ፖርታል (ድረ-ገጽ) ተከፍቶ አገልግሎት ላይ ለማዋል በዝግጅት ላይ እንደሆነ ከቀረበው ጽሑፍ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በተመሳሳይ ኤጀንሲው ከዩኔስኮ ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት በኤጀንሲው የሚሞሪ ኦፍ ዘ ወርልድ ፕሮጀክት ለማካሄድ፣ የሳውንድ አርካይቭስና ቪዲዮ ኮንፈረንስ ለማቋቋም በተደረገው ስምምነት መሠረት የቅድመ ዝግጅት ስራዎች እየተከናወኑና በተለያዩ ፎርማት የሚገኙ የአፐሎግ የድምጽ ቅጅዎችን ወደ ዲጂታል ፎርማት ለመቀየር የሚያስችል የሳውንድ ዲጂታል ስቱዲዮ  የማቋቋም ስራ የተጀመረ መሆኑ በገለጻው ወቅት ተጠቁማል፡፡ በውይይቱም ወቅት የተለያዩ ጥቄዎችና አስተያየቶች ቀርበው በሥራ ሂደቱ ባለሙያዎች መልስና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

በውይይቱ ማጠቃለያ ላይ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር አቶ አትክልት አሰፋ በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂና የመረጃ ሥርዓት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ባለሙያዎች የቀረበው የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት በጣም ጥሩና ሙያዊ መሆኑን ገልፀው ኤጀንሲው ከኢትዮጵያ ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማት ኤጀንሲ ጋር በመተባበር በተቀናጀ የቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት የመረጃ ሥርዓት ማስፋፊያ ላይ እየሠራ ያለው ጠቃሚ ተግባር ተቋሙ ላለሩት

60 ዓመታት ያላገኘውን ዕድል ያገኘበት አጋጣሚ በመሆኑ ለሥራው ትኩረት ሰጥቶ መሠራት ይገባል ብለዋል፡፡

## <u>የመጻሕፍት ስጦታ ተበረከተ</u>

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ በተለያዩ ርዕስ ጉዳዮች ላይ የሚያጠነጥኑና ለተማሪዎች፣ ለተመራማሪዎች፣ ለአጥኚዎችና ለተለያዩ የህ/ሰብ ክፍሎች በመረጃ ምንጭነት የሚያገለግሉ 500 (አምስት መቶ) መጻሕፍትን ለቀይ ሽብር መታሠቢያ ሙዝየም ቤተመጻሕፍት በዕርዳታ ሰጠ፡፡

ኤጀንሲው ለቀይ ሽብር መታሠቢያ ሙዝየም ቤተመጻህፍት ላደረገው የመጻሕፍት ዕርዳታ ነሐሴ 20 ቀን 2002 ዓ.ም የመጻህፍት ስጦታ ርክክብ ሥነ-ስርዓት በሙዝየሙ ቤተመጽሐፍት በተፈጸመበት ወቅት ከቀይ ሽብር ሰማዕታት ቤተሰቦችና ወዳጆች ማህበር ከላቀ ምስጋና ጋር የምስክር ወረቀት ተሰጥቷል፡፡

ኤጀንሲው በ2002 በጀት ዓመት የጥናትና ምርምር እንዲሁም የንባብ ባህልን ለማዳበርና ለማስፋፋት ዓላማው በማድረግ የተለያዩ የመረጃ ሀብቶችን ለ6 የህዝብ አብያተመጻሕፍት ለ9 ክልሎችና ለ2 የከተማ የህዝብ አብያተ መጻሕፍት እንደሰጠ ታውቋል፡፡

## በኤግዚቢሽን ቅድመ ዝግጅት አቀራረብ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ተሰጠ

ነሐሴ 21 ቀን 2002 ዓ.ም በኢጀንሲው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ለግማሽ ቀን “Exhibition over development and Design” በሚል ርዕስ ጉዳዩ በቀጥታ ለሚመለከታቸው የኤጀንሲው ስድስት የሥራ ዘርፎች ባለሙያዎችንና ሠራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ተሰጠ፡፡

የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቱን የሰጡት የደንበኞችና ጥናት ዳይሬክቶሬት ባለሙያ የሆኑት ወ/ሮ ሕሊና ስዩም ናቸው፡፡

በተሰጠው ትምህርት ኤግዝቢሽን ምን ማለት እንደሆነ፣ ስኤግዚቢሽን አይነቶች ኃላማዎች ምን አይነት ነገሮች በኤግዚቢሽን ላይ ሊቀርቡ እንደሚችሉ፣ ስለኤግዚቢሽን አዘገጃጀትና አስተቃቀድ ደረጃዎች፣ አስፈላጊ ቁሳቁሶች፣ የቦታ አመራረጥ አንድን ኤግዚብሽን እንዴት ተወዳጅና ሣቢ ማድረግ እንደሚቻልና በሌሎችም ተዛማጅ ጉዳዮች ዙሪያ ሰፋ ያለ ትምህርት ተሰቷል፡፡

በአንድ ተቋም ኤግዚቢሽን ሲዘጋጅ የቅድመ ኤግዚቢሽን (Pre Exhibition Stage) እና የድህረ ኤግዚቢሽን ግምገማ ደረጃ (Post Exhibition Evaluation Stage) ያሉት መሆኑን ጠቁመው ከዚህ አንፃር ተቋማዊ ኤግዚቢሽኑ ሊዘጋጅ እንደሚገባ ትምህርት አቅራቢዋ አስረድተዋል፡፡

የኤግዚቢሽን ሥራ የአንድ ተቋም የመደበኛ ሥራ አካል እንደመሆኑ ከተለመደውና የዘፈቀደ አሠራር በመውጣት የኤግዚቢሽን አዘገጃጀት ሳይንሳዊ መርሆዎችን ተከትሎ ማዘጋጀት የአንድን ተቋም ዓላማ ከማሳካት በተጨማሪ የሚፈለገውን ውጤት ማስገኘት እንደሚቻል በውይይቱ ማጠቃለያ ተገልጿል፡፡